**የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር /2013**

**የኤሌክትሮኒክ ትራንዛክሽን ለመደንገግ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

ይህ ደንብ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአስፈጻሚ አካላት ሥልጣንና ኃላፊነቶችን በሚዘረዝረው አዋጅ ቁጥር 1097/2010 አንቀጽ 5 እና በኤሌክትሮኒክ ትራንዛክሽን አዋጅ ቁጥር 1205/2013 አንቀጽ 45 መሠረት በሚኒስትሮች ምክር ቤት የወጣ ነው።

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ**

1. **<u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ ደንብ “የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኤሌክትሮኒክ ትራንዛክሽን ደንብ ቁጥር .../2013” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **<u>ትርጓሜ</u>**

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፣

(1) “የአስተዳደር ተቋም” ማለት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት አስፈጻሚ አካል ሆኖ በሕግ የተደራጀ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሲሆን ለፌደራል መንግሥት ተጠሪ የሆነ የከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላትን ይጨምራል፤

(2) “አስተዳደራዊ ውሳኔ” ማለት የዳኝነት ሥልጣን ያላቸው አስፈጻሚ አካላት የሚሰጡት ውሳኔ ነው፤

(3) “አስተዳደራዊ ማኑዋል” ማለት የአስተዳደር ተቋም አዋጆችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን መነሻ በማድረግ የሚያወጣቸው አመላካች መመሪያ ወይም በሌላ ማናቸውም መጠሪያ የሚጠራ ማንኛውም ሰነድ ነው፤

(4) “መመሪያ” ማለት ሕግ አውጪው አካል በሚሰጠው የውክልና ሥልጣን መሠረት አዋጅንና ደንብን መነሻ በማድረግ በአስተዳደር ተቋም የሚወጣና በሰዎች መብት ወይም ጥቅም ላይ ውጤት የሚያስከትል የሕግ ሰነድ ሲሆን በሥራ ላይ ያለ መመሪያን የሚያሻሽል ወይም የሚሽር የሕግ ሰነድንም ይጨመራል፤

(5) "የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሽ" ማለት በኢንተርኔት ወይም በሌላ የመረጃ መረብ አማካኝነት ሸቀጦችን በመሸጥ ወይም አገልግሎቶችን በማቅረብ የንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ሰው ነው፤

(6) "የኤሌክትሮኒክ ንግድ መካከለኛ ፕላትፎርም አንቀሳቃሽ" ማለት በኤሌክትሮኒክ ንግድ ፕላትፎርም አማካኝነት ሸቀጦችን የሚሸጡ ወይም አገልግሎቶችን የሚያቀርቡ የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሾችን በተለያየ ማዕቀፍ አደራጅቶ የሚይዝ ድርጅት ነው፤

(7) "የኤሌክትሮኒክ ንግድ ፕላትፎርም አንቀሳቃሽ" ማለት በኤሌክትሮኒክ ንግድ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች በራሳቸው የንግድ ሥራ ለማካሄድ እንዲችሉ ቀጥታ ተደራሽ የሆኑ ድረገጾችን የሚያቀርብ፣ የሚያቀራርብ፣ ኢንፎርሜሽን የሚለቅና ሌሎች አገልግሎቶችን የሚሰጥ ድርጅት ነው፤

(8) “ሕጎችን በኤሌክትሮኒክ መንገድ ማተም” ማለት ሕጎች መጽደቃቸውን ተከትሎ በአጭር የጊዜ ልዩነት ከሌሎች ጉዳዮች ባሻገር ምልዑነታቸውን ባረጋገጠ መልኩ በአዋጁ አንቀጽ 35 ንዑስ አንቀጽ (3) እና በኤሌክትሮኒክ ፊርማ አዋጅ መሠረት የኤሌክትሮኒክና የቀን ማኅተም አርፎባቸው በሚኒስቴሩ በኤሌክትሮኒክ አግባብ ማተም ነው፤ ይህ ሂደት በወረቀት ላይ የታተመን ሕግ በስካነር ወይም በሌላ አግባብ ኮፒ አድርጎ ማውጣትን አይጨምርም፤

(9) “ምክር ቤት” ማለት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነው፤

(10) “መደበኛ ባልሆነ የንግድ ዘርፍ ላይ የተሰማሩ ሰዎች” ማለት አግባብነት ካለው ተቆጣጣሪ መሥሪያ ቤት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ሳያወጡ በኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሽነት በኤሌክትሮኒክ ንግድ ዘርፍ ላይ የተሰማሩ የተፈጥሮ ሰዎች ናቸው፤

(11) “ኢኮቴ” ማለት የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ነው፤

(12) “ሚኒስቴር” ወይም “ሚኒስትር” ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

(13) “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

(14) “አዋጅ“ ማለት የኤሌክትሮኒ ትራንዛክሽን አዋጅ ቁጥር 1205/2012 ነው፤

(15) “የመንግሥት ተቋም” ማለት የፌደራል መንግሥት እና የክልል መንግሥታት አስፈጻሚ አካል ሆኖ በሕግ የተደራጀ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሲሆን ለፌደራል መንግሥት ተጠሪ የሆነ የከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላትን ይጨምራል፤

(16) “ተያያዥ ሽያጭ” ማለት ሸማች ከሻጭ ሊገዛ የሚፈልገውን ሸቀጥ ማግኘት የሚችለው ከዛው ሻጭ ላይ ሌላ ሸቀጥ የገዛ እንደሆነ ብቻ ነው በማለት የሚደረግ በሸማችና ሻጭ መካከል የሚደረግ የሽያጭ ውል ዓይነት ነው፤

(17) “የሥራ ቡድን” ማለት የኤሌክትሮኒክ መንግሥት መድረክ እና የመንግሥት ተቋማት የኢኮቴ ዳይሬክተሮች ኮሚቴን ጨምሮ በአዋጁ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (5) እና በዚህ ደንብ መሠረት የተቋቋመ፣ እና ተጠሪነቱ ለብሔራዊ የዲጂታል ኢኮኖሚ ምክር ቤት የሆነ አደረጃጀት ነው፤

(18) ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው ድንጋጌ የሴትንም ይጨምራል።

## 3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

(1) ይህ ደንብ፤

(ሀ) ለሕዝብ አገልግሎት የመስጠት ሥልጣንና ተግባር ባላቸው የፌዴራል እና የክልል መንግሥታት፣ የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተሞች ተቋማት ላይ፣ እንደዚሁም፣

(ለ) በኤሌክትሮኒክ ንግድ፣ በኤሌክትሮኒክ የመንግሥት አገልግሎት፣ በኤሌክትሮኒክ መልዕክቶች እና በሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች ላይ፣

ተፈጻሚ ነው።

(2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ አዋጅ፤

(ሀ) ጋብቻና ፍቺን ጨምሮ ከግላዊ ሁኔታ ጋር ከተዛመዱ ጉዳዮች፣

(ለ) ከኑዛዜ መስጠት፣ ከኑዛዜ ፎርሞች፣ ኑዛዜን ከመሻር፣ እና ከውርስ አፈጻጸም ጋር በተዛመዱ ጉዳዮች፣

(ሐ) ከፍርድ ቤት ትዕዛዞች፣ መጥሪያዎች፣ የብርበራና የመያዣ ትዕዛዞች እና ሌሎች መሰል ውሳኔዎች፣

(መ) የማይንቀሳቀስ ንብረትን ከማስተለለፍ ጋር በተዛመዱ ጉዳዮች፣ እና

(ሠ) ከህጋዊ የውክልና ጉዳዮች፣

ጋር በተያያዘ ጽሑፍን ወይም የእጅ ፊርማን እንደ ግዴታ በሚወስዱ ማናቸውም ሕጎች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።

## 3. <u>የብሔራዊ የዲጂታል ኢኮኖሚ ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባራት</u>

(1) የአዋጁ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (4) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የብሔራዊ የዲጂታል ኢኮኖሚ ምክር ቤት የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች አሉት

(ሀ) ከመደበኛ አሠራር ውጪ በልዩ ሁኔታ የማስተናገጃ ሥርዓትን የተመለከቱ ጉዳዮች፣

(ለ) የንግድ መደብ ስያሜ ያልተሰጣቸው ዘርፎች በጊዜያዊነት የሚስተናገዱበት ሥርዓት፣

(ሐ) የሀገር ውስጥ የንግድ ድርጅቶች በውጭ ሀገር ሲሰማሩ ድጋፍ ማድረግ

(መ) የተለያዩ የመንግስት ኤጀንሲዎችን ለመደገፍ እንዲቻል ሀገራዊ ስትራቴጂዎችን ማቀድ፣ ማዘጋጀት እና የኤሌክትሮኒክ መንግስታዊ እንቅስቃሴዎችን ሁሉ መምራት

(ሠ) የመንግስት አጠቃላይ የቴክኖሎጂ ጉዳዮችን፣ ፖሊሲዎችን እና ህጎችን ማልማት፣ ትንተና እና ግምገማ ውስጥ መሳተፍ

(ረ) የኤሌክትሮኒክ መንግስት ጣልቃ ገብነት፣ የትኩረት አቅጣጫዎች ላይ መወሰን እና በኤሌክትሮኒክ መንግስት እሳቤዎች እና ፕሮጀክቶች ላይ ማተኮር

(ሰ) የኤሌክትሮኒክ መንግስት መካከለኛ እና የረጅም ጊዜ እቅድን ማፅደቅ

(ሸ) ለኤሌክትሮኒክ መንግስት ልማት፣ ጥገና፣ ዘላቂነት እና መስፋፋት ሚያስፈልግ የበጀት ድርሻ መጠን በእያንዳንዱ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች መወስኑ

(2) የአዋጁ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (5) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ምክር ቤቱ የሥራ ቡድኖችን የሚያማክሩ አካላትን ከግሉ ሴክተር መመልመል ይችላል።

## 4. <u>ቋንቋ</u>

(1) የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሾች፣ የኤሌክትሮኒክ ንግድ መካከለኛ ፕላትፎርም አንቀሳቃሾችና የኤሌክትሮኒክ ፕላትፎርም አንቀሳቃሾች እንደዚሁም የመንግሥት ተቋማት የሚሰጡትን አገልግሎቶች የተመለከቱ መረጃዎች በሚፈልጉት ቋንቋ ማውጣት ይችላሉ።

(2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) የተቀመጠው ጠቅላላ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሾች፣ የኤሌክትሮኒክ ንግድ መካከለኛ ፕላትፎርም አንቀሳቃሾችና የኤሌክትሮኒክ ንግድ ፕላትፎርም አንቀሳቃሾች እንደዚሁም የመንግሥት ተቋማት ከሚመርጧቸው ቋንቋዎች በተጨማሪ እንዳግባብነቱ

(ሀ) የፌደራል መንግሥት የሥራ ቋንቋን፣ ወይም

(ለ) የክልል የሥራ ቋንቋን

መጠቀም አለባቸው።

**5. ምዝገባ**

(1) የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሾች፣ የኤሌክትሮኒክ ንግድ ፕላትፎርም አንቀሳቃሾችና የኤሌክትሮኒክ ንግድ መካከለኛ ፕላትፎርም አንቀሳቃሾች ሚኒስቴሩ ዘንድ ቀርበው መመዝገብ አለባቸው።

(2) ከሌሎች ቅድመ ሁኔታዎች ባሻገር የሚከተሉት ማስረጃዎች፣ ማለትም

(ሀ) የግብር ከፋይ ቁጥር ሠርተፊኬት፤

(ለ) የ<ዶት ኢቲ> ዶሜይን ስም ምዝገባ፤

(ሐ) የኤሌክትሮኒክ ትራንዛክሽን የኤሌክትሮኒክ መልዕክት ኮሙኒኬሽን ድንጋጌዎችን ለማክበር የሚያስችል ሥርዓት የዘረጋ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ፤

(መ) የንግድ ድርጅቱ ለደንበኞቹ የሚያቀርበው ረቂቅ የውል ሰነድ (ደንብና ግዴታ)፤

(ሠ) የድሮፕ ሺፒንግ አገልግሎት ከሚሰጡ ድርጅቶች ውጪ የፈጣን መልዕክት የማድረስ ሥራ ከሚሠራ ድርጅት ጋር ያላቸው ውል፤

(ረ) የዘረጉት የኤሌክትሮኒክ የክፍያ ሥርዓት አግባብነት ባለው ተቆጣጣሪ መሥሪያ ቤት ዕውቅና ያለው ስለመሆኑ ማስረጃ

ለምዝገባ ማቅረብ አለባቸው።

(3) በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ቢኖርም፣ ሚኒስቴሩ ተጨማሪ ቅድመ ሁኔታዎችን መወሰን ይችላል።

**6. የንግድ ምዝገባና ፈቃድ**

(1) የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሾች፣ የኤሌክትሮኒክ ንግድ ፕላትፎርም መካከለኛ አንቀሳቃሾች እና የኤሌክትሮኒክ ንግድ ፕላትፎርም አንቀሳቃሾች አግባብነት ባላቸው ሕጎች ውስጥ በተመለከተው መሠረት በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ ሒደት ውስጥ ማለፍ አለባቸው።

(2) በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሽነት መደበኛ ባልሆነ የኢኮኖሚ ዘርፍ የተሰማሩ የተፈጥሮ ሰዎች የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ማውጣት አያስፈልጋቸውም።

## ክፍል ሁለት
## የኤሌክትሮኒክ ንግድ

## ንዑስ ክፍል አንድ
## የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሽ

### 7. በኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሾች ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑ መርሆዎች

(1) የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሾች የንግድ ሥራዎቻቸውን በተመለከተ ከሌሎች ባሻገር

(ሀ) ለፈቃደኝነት፣ ለዕኩልነት፣ ለፍትሐዊነትና ለቅንልቡና መርሆች ተገዥ መሆን፣

(ለ) ሕጎችንና የንግድ ሥነ-ምግባርን ማክበር፣

(ሐ) በገበያ ውድድር ውስጥ በፍትሃዊነት መሳተፍ፣

(መ) ለምርቶችና አገልግሎቶች ጥራት ኃላፊነት መውሰድ፣ እንደዚሁም

(ሠ) በሚመለከታቸው አካላት ለሚደረግ ቁጥጥር ተገዥ መሆን

አለባቸው።

(2) የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሾች በኤሌክትሮኒክ ንግድ ፕላትፎርም አንቀሳቃሾች የወጣውን የሥነ-ምግባር ደንብ ማክበር አለባቸው።

(3) የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሾች የዘርፍ ማኅበራት የራሳቸውን የዘርፍ ሥነ-ምግባር ደንቦች ማውጣትና፣ የዘርፉ ሥነ-ምግባርን እንዲከበር ማድረግ አለባቸው።

### 8. የግብር ግዴታ

የንግድ ሥራቸውን በኢንተርኔት ወይም በሌላ የመረጃ መረብ አማካኝነት የሚያከናውኑና መደበኛ ባልሆነ የንግድ ዘርፍ ላይ የተሰማሩ ሰዎችን ጨምሮ፣ የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሾች የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የማውጣት ግዴታ አለባቸው።

### 9. የደረጃዎች ተስማሚነት

(1) በኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሾች የሚሸጡ ዕቃዎች ወይም የሚሰጡ አገልግሎቶች አግባብነት ባለው ዘርፍ ከተቀመጡ ደረጃዎች ጋር ተስማሚ መሆን አለባቸው።

(2) የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሾች በሕግ የተከለከሉ ዕቃዎች ሽያጭ ወይም አገልግሎቶች አቅርቦት ላይ መሰማራት የተከለከለ ነው።

(3) በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተቀመጡ ግዴታዎች መደበኛ ባልሆነ የንግድ ዘርፍ ላይ የተሰማሩ ሰዎች ላይ ተፈጻሚ ነው።

### 10. ደረሰኞች

(1) ዕቃዎች በሚሸጡበት ወይም አገልግሎቶች በሚሰጡበት ጊዜ የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሾች አግባብነት ባለው ሕግ በተደነገገው መሠረት የወረቀት ወይም የኤሌክትሮኒክ ደረሰኞችን ወይም ሌሎች የሽያጭ ማረጋገጫዎችን መስጠት አለባቸው።

(2) የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሾች ሸማቾች ክፍያ ከመፈጸማቸው በፊት የክፍያ ማረጋገጫ ደረሰኙ ቅርጽ ከወረቀት ወይም ከኤሌክትሮኒክ አግባብ የትኛውን እንደሚመርጡ መጠየቅ አለባቸው።

## 11. ሕጋዊነትን የተመለከቱ መረጃዎች

(1) የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሾች ከሌሎች መረጃዎች ባሻገር በኤሌክትሮኒክ ትራንዛክሽን አዋጅ የተደነገገውን መረጃ እንደዚሁም ከንግድ ምዝገባና ፈቃድ አሠጣጥ ጋር የተያያዙ መረጃዎችን በድረ ገጻቸው ወይም ሌላ አቻ የመረጃ ገጽ ላይ ግልጽ በሆነ ሥፍራ የማተም ወይም ይህ መረጃ ሊገኝ የሚችልበትን ሊንክ ማስቀመጥ አለባቸው።

(2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) ላይ የተጠቀሰው መረጃ ከተለወጠ፣ የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሾች ይህንኑ ማስተካከልና በጊዜው ማተም አለባቸው።

(3) የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሽ የሥራ ዕንቅስቃሴውን ለማቆም ካቀደ አግባብነት ያላቸው መረጃዎችን የሥራ ዕንቅስቃሴውን ከማቆሙ በፊት ባሉ 30 ቀናት ውስጥ በድረገጹ ወይም ሌላ አቻ የመረጃ ገጽ የመነሻ ገጽ ላይ ለዕይታ በሚመች ቦታ ላይ ማተም አለበት።

## 12. ምርትና አገልግሎትን የተመለከቱ መረጃዎች

(1) የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሾች የምርቶቻቸውን ወይም የአገልግሎቶቻቸውን ዝርዝር መረጃ በአጠቃላይ፣ በታማኝነት፣ በትክክልና በጊዜ የመስጠት ግዴታ አለባቸው።

(2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) ላይ የሚሰጥ መረጃ ሸማቾች መብታቸውን ለማስፈጸም የሚያስችላቸው መሆን አለበት።

(3) የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሾች ሃሰተኛ ወይም የተዛቡ የንግድ መረጃዎችን ከመስጠት መታቀብ አለባቸው።

(4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (3) ላይ የተጠቀሱት የተዛቡ መረጃዎች፣ ከሌሎች ጉዳዮች ባሻገር ሳይፈጸሙ እንደተፈጸሙ የሚቀርቡ ሽያጮችን የተመለከቱና ሸማቾች ያልሰጡትን አስተያየት እንደሰጡ አድርጎ ማቅረብን ይጨምራል።

## 13. ፕሮፋይሎችን መሠረት አድርገው የፍለጋ ውጤቶችን ስለማሳየት

(1) የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሾች የሸማቾችን ጠባይ፣ ፍላጎቶች፣ የሸመታ ልምድና ሌሎች ባሕሪያትን መሠረት በማድረግ ሸማቾች የዕቃዎችን ወይም የአገልግሎቶችን ግዥ እንዲፈጽሙ የሚያስችሉ የፍለጋ ውጤቶች የሚያቀርቡ ከሆነ፣ የሸማቾቹን መብቶች ሙሉ በሙሉ እንደሚያከብሩ ለሸማቾቹ መረጃ የመስጠት ግዴታ አለባቸው።

(2) ለሸማቾች ማስታወቂያዎችን የሚልኩ የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሾች አግባብነት ያላቸውን ሕጎች መከተል አለባቸው።

## 14. ተያያዥ ሽያጭ

(1) የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሾች ተያያዥ የዕቃዎች ወይም የአገልግሎቶች ሽያጭ በሚያከናውኑበት ጊዜ ሸማቾችን አመቺ በሆነ መንገድ ማሳወቅ አለባቸው፡፡

(2) ተያያዥ ሽያጭ እንደነባሪ አማራጭ መቀመጥ የለበትም፡፡

## 15. ሸቀጦችንና አገልግሎቶችን ማድረስ

(1) የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሾች ከሸማቾች ጋር በተስማሙበት አግባብና የጊዜ ገደብ ሸቀጦችን ወይም አገልግሎቶችን ማድረስ አለባቸው።

(2) የዚህን ደንብ ተፈጻሚነት ለማረጋገጥ የሚወጣው መመሪያ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገውን መርህ ተፈጻሚነት የሚገድቡ ዝርዝር ሁኔታዎችን ሊደነግግ ይችላል።

(3) በሌላ መልክ ስምምነት ካልተደረገ በስተቀር፣ የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሾች ከትራንስፖርት ሒደት ጋር ተያያዥ የሆኑ ኃላፊነቶችን የመውሰድ ግዴታ አለባቸው።

(4) ሸማቹ የመልዕክት አስተላላፊ ወይም የሎጅስቲክስ አገልግሎት ሰጪን ከመረጠ የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሾች በዚህ አንቀጽ በንዑስ-አንቀጽ (2) ላይ ከተመለከተው ግዴታ ነጻ ይሆናሉ።

## 16. የቅድሚያ ክፍያ

(1) ስምምነት በተደረገበት መሠረት የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሾች ከሸማቾች የማስያዣ ገንዘብ የሚሰበስቡ ከሆነ የማስያዣ ገንዘቡ የሚመለስበትን መንገድና አሠራር በግልጽ ማስቀመጥ አለባቸው፤ የማስያዣ ገንዘቡን ለመልቀቅ ተገቢ ያልሆኑ ቅድመ ሁኔታዎችን ማስቀመጥ የተከለከለ ነው።

(2) ሸማቾች ለማስያዣ ያስቀመጡት ገንዘብ እንዲመለስላቸው ከጠየቁ የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሾች ተቀማጭ ገንዘቡን በደንብና ግዴታዎች ላይ በተገለጸው ጊዜ መመለስ አለባቸው።

(3) ከኤሌክትሮኒክ ንግድ ጋር በተያያዙ የሚደረጉ ክፍያዎች አግባብነት ያላቸው ሕጎችን የተከተሉ መሆን አለባቸው።

## 17. የገበያ ድርሻን በአሉታዊ መንገድ መጠቀም

(1) የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሽ ከሌሎች ምክንያቶች ባሻገር በቴክኖሎጂ ብቃት፣ በደንበኛ ብዛት፣ አግባብነት ያላቸው ኢንዱስትሪዎችን ለመቆጣጠር ባለው አቅም፣ እንደዚሁም ሌሎች አንቀሳቃሾች ለንግድ ሥራቸው በእርሱ የሚደገፉ ከሆነ፣ በገበያው ውስጥ ያለውን ተጽዕኖ ፈጣሪነት በመጠቀም የገበያ ውድድርን ማጥፋት ወይም መገደብ የተከለከለ ነው።

(2) በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው አጠቃላይ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አግባብነት ያላቸው ሕጎች ተፈጻሚ ይሆናሉ።

## 18. የግል መረጃዎች ጥበቃ

(1) የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሾች የሸማቾችን የግል ዳታ የሚሰበስቡ ወይም የሚጠቀሙ ከሆነ የግል ዳታ ጥበቃን በተመለከተ የወጡ ሕጎችንና አስተዳደራዊ መመሪያዎችን መከተል አለባቸው።

(2) ሸማቾች የግል ዳታቸው ማቀናበርን በተመለከተ ካደረጓቸው ስምምነቶች መውጣት እንዲችሉ ዕድል መሰጠት አለበት፤ ይህ ሒደት ውስብስብ መሆን የለበትም።

(3) አግባብነት ባለው ሕግ በተቃራኒ ካልተደነገገ በስተቀር፣ ሸማቾች የግል ዳታቸው ማቀናበርን በተመለከተ ካደረጓቸው ስምምነቶች ሲወጡ የግል ዳታቸው ወዲያውኑ መሰረዝ አለበት።

## 19. ድንበር ተሻጋሪ ንግድ

በድንበር ተሻጋሪ የኤሌክትሮኒክ ንግድ ላይ የተሰማሩ የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሾች በገቢና ወጪ ንግድ ሕጎችና አግባብነት ባላቸው ሌሎች አግባብነት ላላቸው ሕጎች ተገዥ መሆን አለባቸው።

## 20. የሸማቾች መብት ጥበቃ ድንጋጌዎች

(1) የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሾች ከሌሎች ባሻገር፣

(ሀ) የቴክኒክ መስፈርቶችን ካሉ እነርሱን ጨምሮ ሸቀጦቹንና አገልግሎቶቹን በተመለከተ ፍትሃዊና ትክክለኛ የሆነ መግለጫ የማቅረብ፣

(ለ) የታክስና የማጓጓዣ ክፍያዎችን ጨምሮ የያንዳንዱ ዕቃ ወይም አገልግሎት የዋጋ ዝርዝር፣

(ሐ) የጉምሩክ ቀረጥ ወይም የድለላ ክፍያዎችን ጨምሮ መከፈል ያለበት ወይም ምናልባት የሚያስከፍል ተጨማሪ ክፍያ ዝርዝር እና የሚታወቅ ከሆነ የክፍያው መጠን፣

(መ) አግባብነት ካለው፣ ከሚከፈለው የገንዘብ መጠን በተጨማሪ የግብይቱ ጠቅላላ ተከፋይ መጠን እንደዚሁም የክፍያው የድግግሞሽ መጠን፣

(ሠ) የክፍያ ሁኔታዎችና መንገዶች፣

(ረ) አግባብነት ካለው፣ ሸቀጡ ወይም አገልግሎቱ ርክክብ የሚደረግበት አድራሻ፣ ቀን፣ የማጓጓዣ ዋጋና መንገድ፣

(ሸ) የተያያዥ ንግድ ስምምነት የተካተተ ከሆነ፣ የተያያዥ ንግዱ ስምምነት ዝርዝርና የተያያዥ ንግዱ የክፍያ መጠን፣

(ቀ) ዋጋዎቹ የተገለጹት በኢትዮጵያ ብር ካልሆነ፣ አግባብነት ባለው መንግሥታዊ ተቋም ተቀባይነት ያገኘ የውጪ ምንዛሪ፣ እንደዚሁም

(በ) በኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሹ የሚጣሉ ማናቸውም ሌሎች ክልከላዎች፣ ገደቦችና ሁኔታዎች የማተም ግዴታ አለባቸው።

(2) ሽያጩ የሚደረግበት ጉዳይ አገልግሎት ለመስጠት ከሆነ፣ የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሾች በዚህ አንቀጽ በንዑስ-አንቀጽ (1) ከተመለከተው የመረጃ ዝርዝር በተጨማሪ፣

(ሀ) አገልግሎቱ የሚጀምርበት፣ የሚቀጥልበትና የሚጠናቀቅበት ቀንን (ቀናትን)፣

(ለ) ተገቢነት ካለው፣ አገልግሎቱ የትና እንዴት እንደሚከናወን፣ እንደዚሁም

(ሐ) አገልግሎቱ የሚሰጠው አንቀሳቃሹን በሚወክል በሌላ ሰው ከሆነ፣ አገልግሎቱን የሚሰጠው ሰው ስምን የሚገልጽ መረጃ የመስጠት ግዴታ አለባቸው

## 21. የመቀበል ወይም ውድቅ የማድረግ ዕድል

የኦንላይን ግዥን ከመፈጸሙ በፊት ሸማቹ ስህተቶችን እንዲያርምና ስምምነቱን እንዲቀበል ወይም ውድቅ እንዲያደርግ ዕድል ሊሰጠው ይገባል።

## 22. የጽሑፍ ስምምነት

(1) የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሹ ሸቀጡን ወይም አገልግሎቱን በሚያስረክብበት ጊዜ የውሉን ቅጅ በጽሑፍ ለሸማቹ መስጠት አለበት።

(2) የውል ቅጅው ለሸማቹ በኤሌክትሮኒክ አግባብ የሚቀርብ ከሆነ፣ የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሹ ሸማቹ የውል ቅጅውን ራሱ ጋር በማስቀመጥ፣ በማተምና ዳውንሎድ በማድረግ በቀጣይ እንዲገለገልበት በሚያስችል አግባብ የተደራጀ መሆኑን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት።

## ንዑስ ክፍል ሁለት
## የኤሌክትሮኒክ ንግድ ፕላትፎርም አንቀሳቃሾች

## 23. መረጃ መሰብሰብ

(1) የኤሌክትሮኒክ ንግድ ፕላትፎርም አንቀሳቃሾች በፕላትፎርሙ ላይ ሸቀጦችን ለመሸጥ ወይም አገልግሎቶችን ለማቅረብ ጥያቄ የሚያቀርቡ የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሾች በአዋጁ መሠረት የተሟላ መረጃ እንዲያቀርቡ መጠየቅ፣ መረጃውን ማደራጀት፣ ወቅታዊ ማድረግና በየጊዜው ይዘቱን ማረጋገጥ አለባቸው።

(2) የኤሌክትሮኒክ ንግድ ፕላትፎርም አንቀሳቃሾች የኤሌክትሮኒክ ንግድ መካከለኛ ፕላትፎርም አንቀሳቃሾችን በተመለከተ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) ላይ የተመለከቱት ግዴታዎች አሉባቸው።

## 24. የመተባበር ግዴታ

(1) የኤሌክትሮኒክ ንግድ ፕላትፎርም አንቀሳቃሾች በፕላትፎርማቸው ላይ ሸቀጥ የሚሸጡና አገልግሎት የሚያቀርቡ የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሾችን ማንነት በተመለከተ መረጃዎችን አግባብነት ላላቸው ተቆጣጣሪ ተቋማት የመስጠት ግዴታ አለባቸው።

(2) የኤሌክትሮኒክ ንግድ ፕላትፎርም አንቀሳቃሾች በፕላትፎርሙ ላይ ለሽያጭ የቀረቡ ሸቀጦችና አገልግሎቶችን አስመልክቶ የቀረቡ መረጃዎች የዚህን ደንብ ወይም የማንኛውንም ሌላ ሕግ ድንጋጌዎች የሚጥስ ከሆነ፣

(ሀ) በሕጎቹ መሰረት አስፈላጊ እርምጃዎችን መውሰድ፣ እና

(ለ) ለሚመለከተው መንግሥታዊ ተቋም ሁኔታውን የማሳወቅ ግዴታ

አለባቸው።

## 25. የኔትወርክና የሳይበር ደህንነት

(1) የኤሌክትሮኒክ ንግድ ፕላትፎርም አንቀሳቃሾች የኤሌክትሮኒክ ትራንዛክሽኖችን ደህንነት ለማረጋገጥ የቴክኒክ እርምጃዎችን ጨምሮ አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን መውሰድ አለባቸው።

(2) የኤሌክትሮኒክ ንግድ ፕላትፎርም አንቀሳቃሾች ሊያጋጥሙ የሚችሉ የሳይበር ጥቃቶችን በተመለከተ የመጠባበቂያ ዕቅድ ማውጣት፣ እንዳስፈላጊነቱ ይህንኑ የመተግበርና ለሚመለከተው መንግሥታዊ ተቋም ሁኔታውን የማሳወቅ ግዴታ አለባቸው።

## 26. መረጃ መሰብሰብና ጠብቆ ማቆየት

(1) የኤሌክትሮኒክ ንግድ ፕላትፎርም አንቀሳቃሾች መረጃ መመዝገብና ጠብቆ ማቆየት እንደዚሁም መረጃዎቹ ምሉዕ፣ ምስጢራዊነቱ የተጠበቀና ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው።

(2) የአገልግሎቶቹና የግብይቶቹ መረጃ ግብይቶቹ ከተጠናቀቁበት ቀን አንስቶ ቢያንስ አግባብነት ባላቸው ሕጎች ለተደነገገው የጊዜ ገደብ ያህል መያዝ ይኖርበታል።

## 27. ሊከተሏቸው የሚገቡ መርሆች

(1) የኤሌክትሮኒክ ንግድ ፕላትፎርም አንቀሳቃሾች የግልጽኝነት፣ የፍትሃዊነትና የዕኩልነት መርሆዎችን መከተል አለባቸው።

(2) የአገልግሎት ስምምነቱና የሥነ-ምግባር ደንቡ ከሌሎች ጉዳዮች ባሻገር

(ሀ) ፕላትፎርሙን ከመጠቀምና ከማቋረጥ ጋር የተያያዙ መብትና ግዴታን፣

(ለ) የሸቀጦችና የአገልግሎቶች የጥራት ማረጋገጫን፣

(ሐ) የሸማቾች መብቶች ጥበቃን፣ እና

(መ) የግል ዳታ ጥበቃን

የተመለከቱ መረጃዎችን መያዝ አለባቸው።

## 28. የውሎችንና የሥነ-ምግባር ደንብን ማተም

(1) የኤሌክትሮኒክ ንግድ ፕላትፎርም አንቀሳቃሾች የውል ስምምነታቸውን እና የሥነምግባር ደንቦቻቸውን ማተም ወይም እነዚህ ሰነዶች የሚገኙባቸውን ሊንኮች የሚገልጹ መረጃዎች በድረገጻቸው ወይም ሌላ አቻ የመረጃ ገጽ ላይ በግልጽ በሚታይ ቦታ ማስቀመጥ፣ እንደዚሁም የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሾችንና ሸማቾች

በተመቻቸ መንገድና ሙሉ በሙሉ ሊያነቡና ወደራሳቸው የኤሌክትሮኒክ መሳሪያ ሊያወርዱ የሚችሉበትን መንገድ ማረጋገጥ አለባቸው።

(2) የውል ስምምነታቸውን እንደዚሁም የሥነምግባር ደንቦቻቸውን ሲከልሱ ከተጠቃሚዎች አስተያየት መሰብሰብ አለባቸው።

(3) የተከለሰው ይዘት ተግባራዊ ከመሆኑ ቢያንስ ከሰላሳ ቀናት በፊት ለሕዝብ ግልጽ እንዲሆን መታተም ይኖርበታል።

## 29. ከኤሌክትሮኒክ ንግድ መካከለኛ ፕላትፎርም አንቀሳቃሾች ጋር ያሉ ግዴታዎች

የኤሌክትሮኒክ ንግድ ፕላትፎርም አንቀሳቃሾች በኤሌክትሮኒክ ንግድ መካከለኛ ፕላትፎርም አንቀሳቃሾች ላይ ተገቢ ያልሆኑ ግዴታዎችን መጣል የተከለከለ ነው።

## 30. ዋስትና

(1) የኤሌክትሮኒክ ንግድ ፕላትፎርም አንቀሳቃሾች የኤሌክትሮኒክ ንግድ ዕድገትንና የሸማቾች መብት ጥበቃን የሚያጎለብት የዕቃዎችና የአገልግሎቶች የጥራት ዋስትና አሠራር የመፍጠር ግዴታ አለባቸው።

(2) የኤሌክትሮኒክ ንግድ ፕላትፎርም አንቀሳቃሾችና የመካከለኛ ፕላትፎርም አንቀሳቃሾች የሸማቾችን መብቶችና ጥቅሞች ለማስጠበቅ ተቀማጭ ገንዘብ ለማስያዝ ስምምነት ካደረጉ ሁለቱም ወገኖች የተሰበሰበውን መጠን፣ የተቀማጭ ገንዘቡን አያያዝ፣ አጠቃቀም፣ የመመለሻ መንገድና የመሳሰሉ ጉዳዮችን በዝርዝር መደንገግ አለባቸው።

(3) የኤሌክትሮኒክ ንግድ ፕላትፎርም አንቀሳቃሾች የካሳ ግዴታን መጀመሪያ እንዲወስዱ ሸማቾች ከጠየቁና የኤሌክትሮኒክ ንግድ ፕላትፎርም አንቀሳቃሾችም ካሳዎችን ከፈጸሙ በኋላ ይህንኑ ከመካከለኛ ፕላትፎርም አንቀሳቃሾች የሚያስመልሱ ከሆነ አግባብነት ያላቸው የሸማቾች መብቶችና ጥቅሞች ጥበቃ ሕጉ ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።

## 31. የግል የንግድ ሥራዎች

(1) የኤሌክትሮኒክ ንግድ ፕላትፎርም አንቀሳቃሾች የራሳቸውን የንግድ ሥራዎች በፕላትፎርማቸው ላይ ማከናወን ይችላሉ።

(2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የኤሌክትሮኒክ ንግድ ፕላትፎርም አንቀሳቃሾች የግል ንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ከሆነ ለዚህ ሥራቸው የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሽ እንደሆኑ ይቆጠራል።

(3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የኤሌክትሮኒክ ንግድ ፕላትፎርም አንቀሳቃሽ የግል ንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ከሆነ ይህን ሥራቸው ከሌላው ሥራቸው በግልጽ ተለይቶ እንዲታወቅ ማድረግ አለባቸው።

**32. ኃላፊነት**

(1) የኤሌክትሮኒክ ንግድ ፕላትፎርም አንቀሳቃሾች በፕላትፎርማቸው ላይ ያሉ የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሾች ለሀገሪቱ ሕጎች ተገዥ መሆናቸውን የማረጋገጥ ግዴታ አለባቸው።

(2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) ላይ የተደነገገው ግዴታ ከተጣሰ የኤሌክትሮኒክ ንግድ ፕላትፎርም አንቀሳቃሾች ከኤሌክትሮኒክ ንግድ መካከለኛ ፕላትፎርም አንቀሳቃሾች ጋር አግባብነት ባላቸው ሕጎች በጋራና በተናጥል ሊጠየቁ ይችላሉ።

**33. የነጥብ አሰጣጥ**

(1) የኤሌክትሮኒክ ንግድ ፕላትፎርም አንቀሳቃሾች የራሳቸውን የነጥብ አሰጣጥ ሥርዓት መፍጠርና ማሻሻል፣ የነጥብ አሰጣጥ መመሪያዎቻቸውን ማተም እንዲሁም በፕላትፎርሙ ላይ የተሸጡትን ዕቃዎች ወይም የቀረቡትን አገልግሎቶች ሸማቾች የሚገመግሙባቸውን መንገዶች ማቅረብ አለባቸው።

(2) የኤሌክትሮኒክ ንግድ ፕላትፎርም አንቀሳቃሾች በፕላትፎርሙ ላይ በተሸጡት ዕቃዎች ወይም በቀረቡት አገልግሎቶች ላይ በሸማቾች የተደረጉ ግምገማዎችን ሸማቾች ሊያገኙ እንዲችሉ ማድረግ አለባቸው።

**34. የፍለጋ ውጤቶችን ስለማሳየት**

(1) የኤሌክትሮኒክ ንግድ ፕላትፎርም አንቀሳቃሾች የሚያቀርቧቸውን የሸቀጥና የአገልግሎት የፍለጋ ውጤቶች ዋጋን፣ የሽያጭ መጠንን፣ የተሰጡ ነጥቦችን እንደዚሁም ሌሎች የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ለሸማቾች ማሳየት አለባቸው።

(2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተዘረዘረው የፍለጋ ውጤት ከምንም ዓይነት ብዥታ የጸዳ መሆን አለበት።

(3) ክፍያ ተፈጽሞባቸው በሸቀጦችና አገልግሎቶች ላይ የተሰጡ አስተያየቶች “ማስታወቂያ” ተብለው መለየት አለባቸው።

**35. የአዕምሯዊ ንብረት መብቶች**

የኤሌክትሮኒክ ንግድ ፕላትፎርም አንቀሳቃሾች የአዕምሮአዊ ንብረት መብቶችን ለማስከበር የሚያስችሉ ደንቦች እንዲኖራቸውና ከአዕምሯዊ ንብረት መብቶች ባለቤቶች ጋር ተባብረው መሥራት አለባቸው።

**36. የሎጂስቲክስ አገልግሎቶችና በማዕከል የሚከወኑ ተግባራት**

(1) የኤሌክትሮኒክ ንግድ ፕላትፎርም አንቀሳቃሾች የሎጅስቲክስ አገልግሎቶችን ማለትም የመጋዘን፣ የክፍያ፣ የዴሊቨሪና መሰል ሌሎች አገልግሎቶችን ለኤሌክትሮኒክ አንቀሳቃሾች ሊሰጡ ይችላሉ።

(2) የኤሌክትሮኒክ ንግድ ፕላትፎርም አንቀሳቃሾች ጨረታን በማዕከል መከወን፣ ወጥ የሆኑ የውል ትራንዛክሽኖች መፈጸምና በማዕከል የሚደረጉ ሽያጮችን ማከናወን የተከለከለ ነው።

## ክፍል ሶስት

## የኤሌክትሮኒክ ውሎች አመሠራረትና አፈጻጸም

### 37. የኤሌክትሮኒክ ውል

(1) ተዋዋይ ወገኖቹ በተቃራኒው ስምምነት ካላደረጉ በስተቀር፣ የኤሌክትሮኒክ ውል እንደተደረገ የሚቆጠረው የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሹ ያተመው የሸቀጡ ወይም የአገልግሎቱ መረጃ ላይ በመመስረት ተጠቃሚው ሸቀጡን ወይም አገልግሎቱን ሲመርጥና በተሳካ ሁኔታ የግዥ ትዕዛዝ ሲሰጥ ነው።

(2) ሸማቹ ክፍያውን ከፈጸመ በኋላ የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሾች መደበኛ የውል ድንጋጌዎችን ወይም ሌሎች መንገዶችን በመጠቀም ውልን ማፍረስ አይፈቀድም።

(3) መደበኛ የውል ድንጋጌዎች በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (2) በተጠቀሰው አግባብ ውልን ለማፍረስ የሚያስችል ድንጋጌ ያካተቱ ከሆነ እነዚህ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ አይሆኑም።

### 38. መረጃን ለተጠቃሚዎች ስለመስጠት

(1) የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሾች ከሌሎች ጉዳዮች ባሻገር ውል የሚመሰርትበትን ሂደት፣ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን፣ ውል ዳውንሎድ የሚደረግበትን አግባብ፤ በግልጽ፣ በዝርዝርና በተብራራ መልክ ለተጠቃሚዎች ማሳወቅ አለባቸው።

(2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) ላይ የተመለከቱት መረጃዎችን ተጠቃሚዎች በአመቺና በተሟላ መልኩ ሊያነቧቸውና ወደራሳቸው የኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎች ሊያወርዷቸው እንደሚችሉ መረጋገጥ አለበት።

(3) ተጠቃሚዎች የግዥ ትዕዛዞችን ከመስጠታቸው በፊት ማንኛውንም ስህተት ማስተካከል እንደሚችሉ የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሾች ማረጋገጥ አለባቸው።

### 39. ጊዜ

(1) ውሉ የተደረገበት ጉዳይ ዕቃዎችን ለማድረስ ከሆነና የዕቃዎቹ ርክክብ የሚደረገው በመልዕክት አስተላላፊና ሎጅስቲክስ ድርጅት ከሆነ የዕቃዎቹ ተቀባይ የፈረመበት ጊዜ የርክክቡ ጊዜ ተደርጎ ይወሰዳል።

(2) ውሉ የተደረገበት ጉዳይ አገልግሎቶችን ለመስጠት ከሆነ በኤሌክትሮኒክ ደረሰኙ ወይም በታተመው ደረሰኝ ላይ የተመለከተው ጊዜ የርክክቡ ጊዜ ተደርጎ ይወሰዳል።

(3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (2) ላይ በተጠቀሰው ደረሰኝ ላይ ጊዜን አስመልክቶ ምንም ዓይነት መረጃ ያልተካተተ ከሆነ ወይም የተጠቀሰው ጊዜ አገልግሎቱ ከተሰጠበት ትክክለኛ ጊዜ ጋር የማይጣጣም ከሆነ አገልግሎቱ የተሰጠበት ትክክለኛ ጊዜ የርክክቡ ጊዜ ተደርጎ ይወሰዳል።

(4) ውሉ የተደረገበት ጉዳይ በኦንላይን ማስተላለፊያ በመጠቀም ርክክብ የተፈጸመበት ከሆነ፣ ውሉ የተደረገበት ጉዳይ በሌላኛው ወገን የኮምፒውተር ሥርዓት የደረሰበት፣ እንደዚሁም ሊፈለግና ሊለይ የሚችልበት ጊዜ የርክክቡ ጊዜ ተደርጎ ይወሰዳል።

(5) ተዋዋዮች የርክክቡን አግባብና ጊዜ በሚመለከት ስምምነት ካላቸው፣ ይህ ስምምነት ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

**40. <u>ዕቃዎችን ማድረስ</u>**

(1) የኤሌክትሮኒክ ንግድ ተዋዋይ ወገኖች ሸቀጦችን በመልዕክት አስተላላፊና በሎጅስቲክስ ድርጅት ለማድረስ ስምምነት ሊያደርጉ ይችላሉ።

(2) የዕቃዎች ርክክብ በሚደረግበት ጊዜ የመልዕክት ማስተላለፍና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ሰጪዎች ዕቃዎቹን በእነርሱ ፊት እንዲፈትሹና እንዲያረጋግጡ ተቀባዮችን ማስገንዘብ አለባቸው። ተቀባዩ ምንም ቅሬታ ከሌለው ዕቃዎቹን ስለመረከቡ መፈረም አለበት።

(3) ወኪሎች ዕቃዎቹን በተቀባዮች ስም የሚረከቡ ከሆነ አገልግሎት ሰጪዎቹ የተቀባዮቹን ስምምነት አስቀድመው ማግኘት አለባቸው።

(4) የመልዕክት ማስተላለፍና የሎጅስቲክስ አገልግሎት ሰጪዎች አገልግሎታቸውን በሚሰጡበት ጊዜ በኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሾች ኃላፊነት ሥር የመልዕክት ተረካቢነት የወኪልነት አገልግሎትን መስጠት ይችላሉ።

**ክፍል አራት**

**በኤሌክትሮኒክ ንግድ ዙሪያ የሚያጋጥሙ**

**አለመግባባቶችን የመፍቻ አግባብ**

**41. <u>የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት</u>**

(1) የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሾች ቅሬታ የማቅረቢያ ሥርዓትን መዘርጋት አለባቸው።

(2) የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሾች ቅሬታዎችን በጊዜ መቀበልና መፍትሔ መስጠት አለባቸው።

**42. <u>አለመግባባትን የመፍቻ አግባቦች</u>**

(1) ከኤሌክትሮኒክ ንግድ ጋር የተያያዙ አለመግባባቶች በድርድር፣ በሽምግልና ወይም በግልግል ሒደቶች ሊፈቱ ይችላሉ።

(2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) ላይ የተመለከተው አለመግባባትን የመፍቻ አግባብ በፍርድ ቤቶች አማካኝነት የሚደረግ ሂደትን አይከለክልም።

**43. <u>ቅራኔዎች በኦንላይን የሚፈቱበት መንገድ</u>**

የኤሌክትሮኒክ ንግድ ፐላትፎርም አንቀሳቃሾች አለመግባባቶችን ለመፍታት የኦንላይን ሥርዓትን ሊዘረጉ፣ ለዚህ የሚሆኑ ደንቦችን ሊያዘጋጁና ሊያትሙ፣ እንደዚሁም በተዋዋይ ወገኖች መካከል የሚነሱ ቅራኔዎችን ፍትሐዊና አድልዎ በሌለበት መንገድ ሊፈቱ ይችላሉ።

**44. <u>የኤሌክትሮኒክ ንግድ ፕላትፎርም አንቀሳቃሾች ሚና</u>**

በኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሽና በሸማች መካከል አለመግባባት በሚፈጠርበት ጊዜ የኤሌክትሮኒክ ንግድ ፕላትፎርም አንቀሳቃሹ የሸማቹን ሕጋዊ መብቶችና ጥቅሞች ለማስጠበቅ ድጋፍ ማድረግ አለበት።

**45. <u>ዋና ሰነዶች</u>**

(1) የኤሌክትሮኒክ ንግድ አለመግባባቶችን ለመፍታት በሚደረጉ ሂደቶች የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሾች የውሎችና የንግድ ሪከርዶች ዋና ቅጆችን ማቅረብ አለባቸው።

(2) የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሾች ከላይ የተጠቀሱት መረጃዎች ከጠፉባቸው፣ መረጃዎቹን በሃሰት ከፈጠሩ፣ ይዘቱን ከነካኩ፣ ካጠፉ፣ ከደበቁ ወይም ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆኑና ይህም ፍርድ ቤቶች፣ የግልግል ዳኝነት ተቋሞች ወይም የሚመለከታቸው ሌሎች ተቋሞችን እውነታዎቹን ለማረጋገጥ እንዳይችሉ ካደረገ የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሹ በዚሁ መሰረት የሕግ ተጠያቂነቶች ይኖሩበታል።

## ክፍል አምስት
## የሕግ ተጠያቂነቶች

**46. <u>የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሾች ኃላፊነቶች</u>**

ሸቀጦችን የሚሸጡ ወይም አገልግሎቶችን የሚሰጡ የኤሌክትሮኒክ ንግድ አንቀሳቃሾች የውል ግዴታዎቻቸውን ካልተወጡ ወይም በሌሎች ላይ ጉዳት ካደረሱ አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት ኃላፊነቶች ይኖሩባቸዋል።

**47. <u>የኤሌክትሮኒክ ንግድ ፕላትፎርም አንቀሳቃሾች ኃላፊነቶች</u>**

የኤሌክትሮኒክ ንግድ ፕላትፎርም አንቀሳቃሾች በአዋጁና በዚህ ደንብ ውስጥ የተመለከተውን ግዴታቸውን ካልተወጡ አግባብነት ባላቸው ሕጎችና በአስተዳደራዊ መመሪያዎች መሠረት ይቀጣሉ።

## ክፍል ስድስት
## የኤሌክትሮኒክ የመንግሥት አገልግሎቶች

## ንዑስ ክፍል አንድ
## የኤሌክትሮኒክ የመንግሥት አገልግሎቶች አሰጣጥ

**48. <u>የኤሌክትሮኒክ የመንግሥት አገልግሎቶች አሰጣጥ ደረጃዎች</u>**

(1) በአዋጁ አንቀጽ 35 ንዑስ አንቀጽ (4) የተደነገገው አጠቃላይ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የመንግሥት ተቋማት የኤሌክትሮኒክ አገልግሎት ሲሰጡ ከሌሎች ባሻገር አገልግሎቱ

(ሀ) የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂዎችን ጥቅም ላይ ያዋለ፣

(ለ) ለዚሁ አገልግሎት የሥራ ሂደቶችን እንደገና የቀየሰ፣

(ሐ) ተዓማኒና ዜጎችን ማዕከል ያደረገ፣

(መ) አግባብነት ያላቸውን የተደራሽነት መስመሮችና ቋንቋዎች ጥቅም ላይ ያዋለ፣

(ሠ) መረጃ ከማግኘትና ከአካል ጉዳተኝነት አንጻር ውስንነት ያለባቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች ጨምሮ ለተገልጋዮች በቂ የድጋፍ አገልግሎቶችን የሚሰጥ፣

(ረ) የኤሌክትሮኒክ ዳታን በዳታው የህይወት ዘመን በሙሉ የሚያስተዳድር፣ እንደዚሁም

(ሰ) የአገልግሎቱን ደሕንነት የሚያረጋግጥ

መሆን አለበት።

(2) የመንግሥት ተቋማት በሚኒስቴሩ የለሙ እና ዕውቅና የተሰጣቸው መተግበሪያዎችን ሥራ ላይ የማዋል ግዴታ አለባቸው።

(3) ሚኒስቴሩ ዝርዝር መስፈርቶችን በተመለከተ በመመሪያ እና እንዳግባብነቱ በጋይድላይን ወይም በሌሎች ሰነዶች መደንገግ ይችላል።

## 49. <u>የኤሌክትሮኒክ የመንግሥት አገልግሎቶች አሰጣጥ አተገባበር</u>

(1) በአዋጁ አንቀጽ 35 ንዑስ አንቀጽ (4) የተደነገገው አጠቃላይ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ሚኒስቴሩ ተጠሪነቱ በአዋጁ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (1) ለተቋቋመው ምክር ቤት የሆነ አደረጃጀት ይፈጥራል።

(2) በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) የሚፈጠረው አደረጃጀት የመንግሥት ተቋማት አገልግሎቶችን በኤሌክትሮኒክ አማራጭ የሚሰጡበትን አግባብ ለማቀናጀት የሚያስችለውን ሥራ ይመራል፣ ይደግፋል፣ ያሳልጣል።

(3) አደረጃጀቱ ተልዕኮውን ለመፈጸም የሚያስችለው የውስጥ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

(4) የመንግሥት ተቋማት በዚህ አደረጃጀት የመሳተፍና የአደረጃጀቱን ውሳኔዎች የመተግበር ግዴታ አለባቸው።

## 50. <u>አደረጃጀት</u>

(1) በአዋጁ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (5) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የኤሌክትሮኒክ የመንግሥት አገልግሎቶችን በተመለከተ

(ሀ) የኤሌክትሮኒክ መንግሥት መድረክ፣ እና

(ለ) የኢኮቴ ዳይሬክተሮች ኮሚቴ

ተብለው የሚጠሩ አደረጃጀቶች ተቋቁመዋል።

(2) በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) የተቋቋሙት አደረጃጀቶች ተጠሪነታቸው በአዋጁ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (1) ለተቋቋመው የብሔራዊ የዲጂታል ኢኮኖሚ ምክር ቤት ነው።

## 51. <u>የኤሌክትሮኒክ መንግሥት መድረክ አወቃቀር</u>

(1) የኤሌክትሮኒክ መንግስት መድረክ

(ሀ) ሚኒስትር ዴኤታዎች፣

(ለ) ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች ውጪ ያሉ የመንግሥት ተቋማት የበላይ አመራሮች፣

(ሐ) የግሉ ዘርፍ እና የሲቪል ማኅበራት ተወካዮች

አባላት በመሆን በሚኒስትሩ ይዋቀራል።

(2) የኤሌክትሮኒክ መንግስት መድረክ አባላት ቁጥራቸው እንደ አስፈላጊነቱ በሚኒስቴሩ ይወሰናል።

## 52. የኤሌክትሮኒክ መንግሥት መድረክ ተግባርና ኃላፊነት

(1) የኤሌክትሮኒክ የመንግሥት አገልግሎቶች መድረክ

(ሀ) የተለያዩ የመንግሥት ተቋሞችን የሚያማክሉ ትልልቅ የኤሌክትሮኒክ መንግሥት ፕሮጀክቶችን ዕቅድ የመተንተን፤

(ለ) ብሔራዊ የዲጂታላይዜሽን አጀንዳ የመቅረጽ፣

(ሐ) የኤሌክትሮኒክ መንግሥት አጠቃቀም ፍላጎት ጥናት የማስጀመር፣

(መ) ትስስር የሚያጠናክሩ መንግስታዊ ፕሮጀክቶችን የመደገፍ፣

(ሠ) የመመዘኛ ደረጃዎችን ማልማት፣ ማበልጸግ፣ የጋራ ኢንተርፕራይዝ አርኪቴክቸር መቋቋምን እና መጠቀምን የማረጋገጥ

ተግባርና ኃላፊነቶች አሉት።

(2) በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው አጠቃላይ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የኤሌክትሮኒክ የመንግሥት አገልግሎቶች መድረክ በብሔራዊ የዲጂታል ኢኮኖሚ ምክር ቤት የሚሰጠውን ማንኛውም ተግባር ይፈጽማል።

## 53. የኢኮቴ ዳይሬክተሮች ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

(1) የኢኮቴ ዳይሬክተሮች ኮሚቴ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል

(ሀ) ከሚኒስቴሩ ጋር በመመካከርና በመተባበር የኤሌክትሮኒክስ የመንግሥት አገልግሎት መስጫ መተግበሪያዎች ልማትን ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ያስተዋውቃል እንዲሁም ይደግፋል፤

(ለ) የኤሌክትሮኒክ የመንግሥት አገልግሎቶች የተቋም ዓላማዎችን፣ ስትራቴጂካዊ ግቦችን እና ተልዕኮዎችን ለማሳካት ያደረግውን አስተዋጽዖ የሚያሳዩ የአፈፃፀም መስፈርቶችን ያዘጋጃል፤

(ሐ) ከሚኒስቴሩ ጋር በመመካከር የኤሌክትሮኒክ አገልግሎት መተግበሪያዎችን ልማት ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ያስተዋውቃል እንዲሁም ይደግፋል፤

(መ) የተቀናጀ የኤሌክትሮኒክስ መተግበሪያዎችን ለሕዝብ በማዳረስ፣ በመንከባከብ እና በማስተዋወቅ የሚኒስቴሩን ጥረቶችን ይደግፋል፤

(ሠ) የየተቋሙን የኤሌክትሮኒክስ አፈፃፀም ሪፖርት በየሦስት ወሩ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።

(2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ (ሠ) አፈጻጸም፣ ሪፖርቱ

(ሀ) በኤሌክትሮኒክ መንገድ መረጃዎችን ወይም አገልግሎቶችን ያገኙ የተገልጋዮች ብዛት በቁጥር፣ እና

(ለ) ከአጠቃላይ ተገልጋይ ጋር ሲነጻጸር በኤሌክትሮኒክ መንገድ መረጃዎችን ወይም አገልግሎቶችን ያገኙ የተገልጋዮች ብዛት በመቶኛ

ማካተት አለበት።

(3) በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው አጠቃላይ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የብሔራዊ የዲጂታል ኢኮኖሚ ምክር ቤት የሚሰጠውን ማንኛውም ተግባር ይፈጽማል።

## 54. የመንግሥት ተቋም ተግባር እና ኃላፊነት

(1) የመንግሥት መረጃ እና አገልግሎት የተደራጀ እንደአስፈላጊነቱ በበይነመረብ ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት።

(2) ከኤሌክትሮኒክ የመንግሥት አገልግሎት አኳያ የመንግሥት ተቋም ከሚኒስቴሩ ጋር በመተባበር
   (ሀ) የራሱን የኤሌክትሮኒክ የመንግሥት አገልግሎት አተገባበር መንደፍ ፣ መተግበር እና መጠቀም አለበት።
   (ለ) የተቀናጀና በበይነመረብ ላይ የተመሠረተ ሥርዓትን ለማቆየት እና ለማስተዋወቅ ለህብረተሰቡ የመረጃ እና የአገልግሎት ተደራሽነት እንዲኖር ያደርጋል።
   (ሐ) ለዜጎች እንቅስቃሴ አስፈላጊ የሆኑና በይነመረብ ላይ የተመሰረቱ የኤሌክትሮኒክ የመንግሥት አገልግሎቶች ከአንድ ነጥብ እንዲገኙ ያደርጋል።
(3) በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተደነገገው አጠቃላይ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የመንግሥት ተቋም በእጁ የሚገኝ መረጃ አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት የግላዊነት መብትን ባከበረ መልኩ ያቀርባል።

## 55. <u>የኢኮቴ ዳይሬክተሮች ተግባር እና ኃላፊነት</u>

የመንግሥት ተቋሞች የኢኮቴ ዳይሬክተር የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች አሏቸው

(1) ተቋሙ እንዳግባብነቱ ከምክር ቤቱ ወይም ከሚኒስቴሩ ጥሪ ሲቀርብለት፣ በኢኮቴ ዳይሬክተሮች ኮሚቴ ጉባኤ ውስጥ ይሳተፋል፤
(2) የመንግስታዊ አተገባበርን በተለይም የእርስ በእርስ ትስስርን እና መናበብን፣ የመንግስት የኤሌክትሮኒክስ መረጃዎችን ምድብ፣ እና የኮምፒተር ሥርዓት ቅልጥፍናን እና ደህንነትን ይቆጣጠራል፤
(3) የኤሌክትሮኒክ የመንግሥት አገልግሎቶችን በተመለከተ ከሌሎች ጉዳዮች ባሻገር
   (ሀ) የኤሌክትሮኒክ የመንግሥት አገልግሎት የትግበራ ሁኔታ ያለበትን ደረጃ፣
   (ለ) አፈጻጸሙ የተቀመጡ ደረጃዎችን ያከበረ ስለመሆኑ፣ እንደዚሁም
   (ሐ) የመንግሥት ተቋሙ የኤሌክትሮኒክ መንግሥት አገልግሎት አፈፃፀምን የተቋሙን አፈጻጸም ላይ ያመጣው አዎንታዊ ለውጥን

   ያካተተ ሪፖርት በየሩብ ዓመቱ ያቀርባል፤
(4) የመንግስት መረጃዎችን እና አገልግሎቶችን ለማድረስ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ዙሪያ ዘገባ ያጠናቅራል።

## ንዑስ ክፍል ሁለት
## ሕጎችንና ሌሎችን በኤሌክትሮኒክ አግባብ ማተም

## 56. <u>የፌደራል የኤሌክትሮኒክ ነጋሪት ጋዜጣ</u>

(1) በኤሌክትሮኒክ ትራንዛክሽን አዋጅ አንቀጽ 36 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የፌደራሉ መንግሥት አዋጆችና ደንቦች በፌደራል የኤሌክትሮኒክ ነጋሪት ጋዜጣ መታተም አለባቸው።
(2) ሚኒስቴሩ የፌዴራል የኤሌክትሮኒክ ነጋሪት ጋዜጣን ቴክኒካዊ ጉዳዮች ያስተዳድራል።
(3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) ላይ የተጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣት ሚኒስቴሩ አዋጆች በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በጸደቀ በ72 ሰዓታት ውስጥ የአዋጆቹን ሃርድኮፒዎች እና ሶፍትኮፒዎች መሰብሰብ አለበት።
(4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) ላይ የተጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣት ሚኒስቴሩ ደንቦች በሚኒስትሮች ምክር ቤት በጸደቀ በ72 ሰዓታት ውስጥ የደንቦቹን ሃርድኮፒዎች እና ሶፍትኮፒዎች መሰብሰብ አለበት።

## 57. <u>የፌደራል የኤሌክትሮኒክ የሕጎች መዝገብ</u>

(1) በኤሌክትሮኒክ ትራንዛክሽን አዋጅ አንቀጽ 37፣ እንደዚሁም በፌደራል የአስተዳደር ሥነሥርዓት አዋጅ አንቀጽ 16 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የፌደራሉ መንግሥት መመሪያ የሚወጣው በፌደራል የኤሌክትሮኒክ የሕጎች መዝገብ ነው።

(2) በፌደራል የአስተዳደር ሥነሥርዓት አዋጅ አንቀጽ 8 መሠረት የተጣለባቸውን ግዴታ ለመወጣት የአስተዳደር ተቋማት በድንጋጌው የተዘረዘሩት መረጃዎች ከሌሎች አግባቦች ባሻገር በፌደራል የኤሌክትሮኒክ የሕጎች መዝገብ ማውጣት አለባቸው።

(3) በፌደራል የአስተዳደር ሥነሥርዓት አዋጅ አንቀጽ 9 መሠረት የአስተዳደር ተቋማትና ሌሎች ባለድርሻ አካላት አስተያየታቸው ከሌሎች አግባቦች ባሻገር በፌደራል የኤሌክትሮኒክ የሕጎች መዝገብ መሰብሰብ አለባቸው።

(4) ሚኒስቴሩ የፌዴራል የኤሌክትሮኒክ የሕጎች መዝገብ ቴክኒካዊ ጉዳዮችን ያስተዳድራል።

(5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (2) እስከ (4) መሠረት የተጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣት

(ሀ) ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም ረቂቅ መመሪያዎችንና ከእነዚህ ጋር ተያያዥ የሆኑ ማስታወቂያዎችን፣

(ለ) የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ጽ/ቤት በፌደራል የአስተዳደር ሥነሥርዓት አዋጅ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ቁጥር ሰጥቶ የመዘገበውን መመሪያ ቅጅ ከተሰጠው ቁጥር ጋር፣ እንደዚሁም

(ሐ) የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ጽ/ቤት በፌደራል የአስተዳደር ሥነሥርዓት አዋጅ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት የመዘገበውን መመሪያ ቅጅ ከተሰጠው ቁጥር ጋር

ለሚኒስቴሩ ማሳወቅ አለበት።

(6) በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (2) እስከ (5) መሠረት የተጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣት እንዲችል የአስተዳደር ተቋማትና የፌዴራል አቃቤ ሕግ ረቂቅ መመሪያዎችን፣ ከረቂቅ መመሪያዎች ጋር ተያያዥ የሆኑ ማስታወቂያዎችንና የመመሪያዎቹን ሃርድኮፒዎችና ሶፍትኮፒዎችን ለሚኒስቴሩ የማቅረብ ግዴታ አለባቸው።

(7) የመመሪያዎች ቅርጽ የአዋጅና ደንቦችን ቅርጽ የተከተለ መሆን አለበት።

## 58. <u>የፌዴራል አስተዳደራዊ ማኑዋሎች የኤሌክትሮኒክ መዝገብ መቋቋም</u>

(1) በሚኒስትሮች ምክር ቤት ጠባቂነት የሚወጣ የፌዴራል አስተዳደራዊ ማኑዋሎች የኤሌክትሮኒክ መዝገብ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።

(2) የፌዴራል አስተዳደራዊ ማኑዋሎች የኤሌክትሮኒክ መዝገብ የፌዴራል ሕግ አስፈጻሚ አካላትን አስተዳደራዊ ማኑዋሎችን ያትማል።

(3) የአስተዳደራዊ ማኑዋሎቹ የሕትመት ቀን የአስተዳደራዊ ማኑዋሉ የመጨረሻ ይዘት በፌዴራል አስተዳደራዊ ማኑዋሎች የኤሌክትሮኒክ መዝገብ ላይ መጀመሪያ የታተመበት ቀን ይሆናል።

(4) ሚኒስቴሩ የፌዴራል አስተዳደራዊ ማኑዋሎች የኤሌክትሮኒክ መዝገብ ቴክኒካዊ ጉዳዮችን ያስተዳድራል።

(5) በዚህ አንቀጽ በንዑስ-አንቀጽ (4) የተጣለበትን ግዴታ መወጣት ይችል ዘንድ የአስተዳደር ተቋማት አስተዳደራዊ ማኑዋሎቹ ሥራ ላይ ከመዋላቸው አስቀድሞ የአስተዳደራዊ ማኑዋሎቹን ሃርድኮፒዎች እና ሶፍትኮፒዎች ለሚኒስቴሩ የማቅረብ ግዴታ አለባቸው።

**59. <u>የፌዴራል አስተዳደራዊ ውሳኔዎች የኤሌክትሮኒክ መዝገብ መቋቋም</u>**

(1) በሚኒስትሮች ምክር ቤት ጠባቂነት የሚወጣ የፌዴራል አስተዳደራዊ ውሳኔዎች የኤሌክትሮኒክ መዝገብ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።

(2) የፌዴራል አስተዳደራዊ ውሳኔዎች የኤሌክትሮኒክ መዝገብ የዳኝነት ነክ ሥልጣን ያላቸው የአስተዳደር ተቋማትን አስተዳደራዊ ውሳኔዎችን ያትማል።

(3) ሚኒስቴሩ የፌዴራል አስተዳደራዊ ውሳኔዎች የኤሌክትሮኒክ መዝገብ ቴክኒካዊ ጉዳዮችን ያስተዳድራል።

(4) በዚህ አንቀጽ በንዑስ-አንቀጽ (3) የተጣለበትን ግዴታ መወጣት ይችል ዘንድ የአስተዳደር ተቋማት አስተዳደራዊ ውሳኔዎቹ በተሰጡ በ72 ሰዓታት ውስጥ የአስተዳደራዊ ውሳኔዎቹን ሃርድኮፒዎች እና ሶፍትኮፒዎች ለሚኒስቴሩ የማቅረብ ግዴታ አለባቸው።

**ክፍል ሰባት**

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

**60. <u>አስተዳደራዊ ቅጣቶች</u>**

ሚኒስቴሩ ከዚህ ደንብ ድንጋጌዎች ጥሰት ጋር ተያያዥ የሆኑ አስተዳደራዊ ቅጣቶችን በመመሪያ አማካኝነት ይደነግጋል።

**61. <u>መመሪያዎችን የማውጣት ሥልጣን</u>**

ሚኒስቴሩና ሌሎች አግባብነት ያላቸው የመንግሥት ተቋሞች አዋጁንና ይህን ደንብ በሥራ ላይ ለማዋል አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን ሊያወጡ ይችላሉ።

**62. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን አንስቶ የጸና ይሆናል።

**አዲስ አበባ፣...../......./2013 ዓ.ም**

**ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስትር**